**מדינת ישראל**

**משרד החינוך**

סוג הבחינה: בגרות

מועד הבחינה: קיץ תשע"ט, 2019

**מספר השאלון: 022272**

**תרגום לאמהרית (6)**

# היסטוריה

## לעולים חדשים

**הוראות לנבחן**

א. משך הבחינה: שעה וחצי.

ב. מבנה השאלון ומפתח ההערכה:

בשאלון זה פרק אחד ובו ארבע שאלות.

ענה על שתי שאלות.

(50x2) סה"כ — 100 נקודות

ג. חומר עזר מותר בשימוש:

מילון עברי-לועזי / לועזי-עברי.

כתוב במחברת הבחינה בלבד. רשום "טיוטה" בראש כל עמוד המשמש טיוטה.

כתיבת טיוטה בדפים שאינם במחברת הבחינה עלולה לגרום לפסילת הבחינה.

**ההנחיות בשאלון זה מנוסחות בלשון זכר ומכוונות לנבחנות ולנבחנים כאחד.**

**בהצלחה!**

**እስራኤል አገር**

**የትምህርት ሚኒስቴር**

**የፈተናው ዓይነት፦ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት መልቀቂያ ፈተና**

**የፈተናው ወቅት: የ2019 ዓ.ም. የበጋ ፈተና**

**የፈተናው ቁጥር፦ 022272**

**ወደ አማርኛ የተተረጎመ (6)**

# ታሪክ

## ለአዲስ ገቢዎች

**ለተፈታኙ የቀረቡ መመሪያዎች**

א. ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ፦ አንድ ሰዓት ተኩል።

ב. የፈተናው መዋቅርና የነጥብ አሰጣጥ፦

ይህ ፈተና አንድ ምዕራፍ ሲኖረው አራት ጥያቄዎችን ይዟል።

በሁለት ጥያቄዎች ላይ መልስ ስጥ።

(2x50) በአጠቃላይ — 100 ነጥብ

ג. ለመጠቀም የተፈቀደ የመርጃ መሣሪያ፦

የውጭ ቋንቋ-ዕብራይስጥ/ዕብራይስጥ-የውጭ ቋንቋ መዝገበ ቃላት።

በመጠይቁ ደብተር ላይ ብቻ ጻፍ። ለማሰቢያ በምትጠቀምበት ገጽ መግቢያ ላይ በሙሉ "טיוטה" ብለህ ጻፍበት።
ከመጠይቁ ደብተር ውጭ በሆነ ወረቀት ማሰቢያ መጻፍ ለፈተናው ውድቅ መሆን ምክንያት ሊሆን ይችላል።

**በዚህ ፈተና ውስጥ የፈተናው መመሪያዎች በወንድ ጾታ ቢቀርቡም ቅሉ ለሴትም ለወንድም ተፈታኞች ያገለግላሉ።**

**መልካም ዕድል!**

# ጥያቄዎች

## አምባገነኑ መንግሥት (המשטר הטוטליטרי)፣ ናዚነት፣

## ሁለተኛው የዓለም ጦርነትና የይሁዳዊያን መጨፍጨፍ (השואה)

ከ1-4 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ ሁለቱን መልስ (እያንዳንዱ ጥያቄ – 50 ነጥብ)።

**1. ከ1933-1938 ባሉት ዓመታት በናዚ መመሪያዎች ላይ የተሰጡ ምላሾች**

ሀ. የማስታረቂ (פיוס) መመሪያ ምን ነበር?
ለዚህ መመሪያ ሁለት ምክንያቶችን አቅርብ እና ከ1933-1938 ባሉት ዓመታት ከተከሰቱት ክስተቶች ውስጥ በአንዱ እንዴት ተግባራዊ እንደሆነ አሳይ። (25 ነጥብ)

ለ. ናዚዎች ከ1933-1938 ባሉት ዓመታት ውስጥ ፀረ-ይሁዳዊያን መመሪያዎችን በጣሉባቸው ጊዜ የጀርመን ይሁዳዊያን የሰጧቸውን ሁለት ምላሾች አቅርብ።
በዚህ ወቅት ናዚዎች ባወጧቸው ፀረ-ይሁዳዊያን መመሪያዎች ላይ የዓለም ሃገራት የሰጡትን አንድ ምላሽ አብራራ። (25 ነጥብ)

**2. ጀርመን ከማሸነፍ ወደ መሸነፍ**

ሀ. የሪቤንትሮፕ-ሞሎቶቭ (ריבנטרופ־מולוטוב) (1939) ስምምነት ምንድን ነው?
ይህ ስምምነት በሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጀመሪያ ላይ ጀርመንን እንዴት እንደረዳት አብራራ እና በጦርነቱ መጀመሪያ ላይ ጀርመንን ከረዳት ውስጥ ተጨማሪ ምክንያት አቅርብ። (30 ነጥብ)

ለ. ከሚከተሉት ክስተቶች ውስጥ አንዱን ምረጥ፦
- የጀርመን ወደ ሶቭየት ኅብረት ሰብሮ መግባት (ሰኔ/ጁን 1941)
- የአሜሪካ ወደ ጦርነቱ መሳተፍ (ነሐሴ/ኦገስት 1941)

የመረጥከው ክስተት በጦርነቱ ሂደት ላይ ያደረገውን ተፅዕኖ አብራራ። (20 ነጥብ)

**3. በጦርነቱ ጊዜ በይሁዳዊያን ላይ የነበረው የናዚዎች መመሪያ**

ሀ. በፖላንድ የነበሩት ይሁዳዊያን ወደ "ጌቶዎች" ከማለፋቸው **በፊት** ናዚዎች በእነሱ ላይ የነበራቸውን አመለካከት ግለጽ። በመልስህ ላይ ሦስት ምሳሌዎችን አቅርብ።
ለዚህ አመለካከት መንስዔ ከሆኑት አንዱን አብራራ። (25 ነጥብ)

ለ. በዋንሴ ኮንፍረንስ (ስብሰባ) ላይ የተነሱትን ሁለት ርዕሶች አቅርብ (ጥር/ጃንዋሪ 1942)።
በይሁዳዊያን ላይ ያለው የናዚዎች መመሪያ እየባሰ መምጣት (መክፋት) በዚህ ስብሰባ ላይ እንዴት ተግባራዊ እንደሆነ አብራራ። (25 ነጥብ)

**4. ይሁዳውያን በናዚዎች ላይ ያደረጉት ትግል**

ሀ. በ"ሾአ" ወቅት ለነበሩ የአውሮፓ ይሁዳዊያን በእስራኤል አገር የነበሩት የይሁዳዊያን ሠፈራዎች ያደረጉላቸውን ሁለት ድርጊቶች አሳይ። (20 ነጥብ)

ለ. ከፓርቲዛኖች ጋር የተቀላቀሉት ይሁዳውያን የነበሯቸውን ዓላማዎች እና ችግሮች እንዲሁም ከሕብረ ብሔሮች ጦር ጋር የተቀላቀሉት ተዋጊ ይሁዳዊያን የነበሯቸውን ዓላማዎች እና ችግሮች አብራራ። (30 ነጥብ)

**መልካም ዕድል!**

መብቱ የእስራኤል መንግሥት ነው።
መገልበጥም ሆነ ማባዛት እንዲሁም ማሳተም በት/ሚኒስቴር ፈቃድ ብቻ ነው።

**בהצלחה!**

זכות היוצרים שמורה למדינת ישראל
אין להעתיק או לפרסם אלא ברשות משרד החינוך